የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ጤና ቢሮ

BENISHANGUL GUMUZ REGIONAL STATE HEALTH BUREAU

# በጤና ቢሮ የፀረ-ሙስና ጥምረት መገባቢያ ሠነድ

19/12/2017

አሶሳ

# መግቢያ

ሙስና ልማትን በማዳከም የሀገርን እድገት የሚያቀጭጭ፤ የሞራልና የስነምግባር ቀዉስ እንዲባባስ፤ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር የሚያደርግ ፤ለፍትህ መጓደል፤ ለሰብዓዊ መብት ጥሰት፤ ለተፈጥሮና አካባቢ ብክለት ምክንያት የሆነ ዓለም አቀፋዊ ወንጀል ነዉ። ሙስና ደረጃዉ ይለያይ እንጂ በሁሉም የዓለማችን ሀገራት የሚገኝና የሁሉም ሀገራ ተግዳሮት ነዉ። ይሁን እንጂ የችግሩ ዋነኛ ተጠቂዎች እንደአፍሪካ ያሉ ታዳጊ ሀገሮች ናቸዉ። ሀገራችን ኢትዮጵያም የዚህ አደገኛ ወንጀል ተጠቂ ነች።

በመሆኑም ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የስነምግባር እና ፀረ-ሙስና ሥራ ክፍል ከሚያደርገዉ እንቅስቃሴ በተጨማሪ ከሌሎች የስራ ክፍሎች ማለትም ከዉስጥ ኦዲት፣ከህግ ክፍል እና ከመልካም አስተዳደር ጋር የጋራ ቅንጅት በመፍጠር ብልሹ አሰራርን መታገል የሚያስችል የጤና ቢሮ የፀረ-ሙስና ጥምረት እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ነዉ። ጥምረቱ በጋራ በመተባበርና በመቀናጀት በሚደረገዉ እንቅስቃሴም አባላቱ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ተብለዉ እንደ ቢሮ የተለዩ የስራ ክፍሎች ፣ ኃላፊነት የተጣለባቸዉ የስራ ዘረፎችና በሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን  በመከላከል ረገድ ጉልህ ሚና ሊጫወቱ የሚገባቸዉን ሥራ ክፍል በመለየት ይህን ጥምረት ለመጀመር የሚያስችል የጋራ ምክክር በማድረግ መግባባት ላይ ተደርሶ አጭር የሆነ የጋራ እቅድ እንዲነደፍና ማዳበር እንዲቻል ታስቧል።

በዚህም መሠረት የፀረ-ሙስና ጥምረትን ከማርቀቅ ጀምሮ እስከ ማፅደቅ በሚኖረዉ ሂደት የህግ አገልግሎት፤ የዉስጥ ኦዲት፤ የተቋማዊ ለዉጥ፤ የስነምግባርና ፀረ-ሙስና የሚጠበቅባቸዉን ሚና እንዲወጡ በእቅዱ ተካተዋል።

ይህ 4ቱ ጥምረቱ በስነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ዙሪያ ግንዛቤ የመፍጠር ፣ በቢሮ ደረጃ ብሎም በተጣሪ ተቋማት ደረጃ የሚታዩ የሠራተኞች ሥነ-ምግባር ጎደለቶች ላይ እረምጃ ያሰወስዳል ፣ በጋራ የቢሮ ኃላፎዎችን ያማከራሉ፤የዉሳኔ ሀሳቦች ያቅረባሉ፣ ሌሎችም ግልጽነትና ተጣያቂነት የሰፈነበት አሰራርን እንዲሰራ ያሚያደረጉ ሲሆን አባላቱ ለዚሁ ስራ የራሳቸዉን ድርሻ እንደሚወጡ ይጠበቃል። ጥምረቱ የሙስናን ምንነትና የሚያስከትለዉን ዘርፈ-ብዙ ጉዳት ከማወቅና ከመረዳት ባሻገር የሙስናና ብልሹ አሰራር ድርጊቶችን ባለመፈፀም፤ በሌሎች ሲፈፀሙም አምርሮ በመታገልና በማጋለጥ ሙስናን ትርጉም ባለዉ መንገድ ለመታገል ወሳኝ ነዉ። የጥምረቱ አባል የተሰጠዉን ተግባርና ሀላፊነት መወጣት እንዲያስችለዉ ይህ  ሠነድ ተዘጋጅቷል። የሠነዱ ዓላማ፤ ግብ፤ የሚከናወኑ ተግባራት እና የድርጊት መርሃ ግብር  ያካተተ ነዉ።

## የዕቅዱ ዓላማ

- ሁሉም ሰራተኞች በፀረ-ሙስና ትግሉ በንቃት እንዲሳተፉ በማነሳሳት ንቅናቄን መፍጠር ነዉ።

## የዕቅዱ ዝርዝር ዓላማ

- ለሙስና ተጋላጭነታቸዉ የተለዩ ዳይሬክተሮች እንደ ቢሮ ትኩረት በመስጠት የዘርፍ ተጋላጭነት ስጋት ጥናት በማድረግ በስራ ክፍሎቹ ላይ በማትኮር ሙስናን ለመከላከል ሚናቸዉ እንዲጫወቱ ማደረግ፣
- የሥራ ኃላፊዎች የሙስና እና የብልሹ አሰራርን አስከፊ ገፅታ አዉቀዉ ሁሉም ሰራተኞች እንዲገነዘቡ እና ሙስናን እንዲፀየፉ ማድረግ፣
- ሁሉም የጥምረቱ አካላት በፀረ-ሙስና ትግል ዉስጥ የጋራ ግንዛቤ መያዝ ያለዉን ፋይዳ በመረዳት በትግሉ ዙሪያ የተሰባሰቡና ለዚህም አስተዋፅኦ ላላቸዉ ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች፣ መላው ሠራተኞች እና ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን እንዲወጡ ለማስቻል ሥራውን በማስተዋወቅ ንቅናቄ መፍጠር፣
- ጤና ቢሮ እንደሀገር የተደነገገ የስነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ድንጋጌዎችን ተግባራዊ በማድረግ በፀረ-ሙስና ትግሉ አጋርና ንቁ ተሳታፊ መሆኑን በተግባር ማረጋገጥ፣

## ጥምረቱ የሚከናወንበት አግባብ

የጤና ቢሮ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ስራ ክፍል ለመነሻ የሚያቀርበዉን የመወያያ ሰነድ መሰረት በማድረግ ሌላ ስራ ክፍሎች ከራሳቸዉ የስራ ተልዕኮና ባህሪ ጋር በማዋሃድ ሁሉም በሥራ ክፍላቸው ያሉትን ሰራተኞች ስለ ሙስና አስካፊነት ግንዛቤ ያስይዛሉ። እንዲሁም ስራ አስፈፃሚዎቹ የሚከተሉትን ተጨማሪ ተግባራት በራሳቸዉ አቅጣጫ፣ እቅድና ዝግጅት ማከናወን ይችላሉ፣ ስለ አፈፃፀሙም ሪፖርት ያቀርባሉ።

- በስነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ዙርያ ዉይይት ማካሄድ፣
- ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ሂደቶችን እና ምክንያቶቹን መለየት ፣
- የስራ ክፍሉን ዕቅድ ሲያዘጋጁ የሙስና መከላከል ተግባራትን አካቶ ማቀድ፣
- የስራ ክፍሉ ላይ ንቅናቄ ለመፍጠር የሚያስችሉ ሌሎች ሁነቶችን ማከናወን።

## የጥምረቱ ዕቅድ ተፈፃሚ እንዲሆን የባለድርሻ አካላት ተግባር እና ሀላፊነት:—

### የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ስራ ክፍል ተግባር እና ሀላፊነት:

- ሥነ-ምግባርን የመገንባት፣ ሙስናን የመከላከልና የፀረ-ሙስና ትግሉን በኃላፊነት የማስተባበር፣
- ሙስናን የመከላከል ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት የሥነ—ምግባር እና የሞራል እሴቶችን መገንባት፣
- በጤና ቢሮ ውስጥ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲለዩና እንዲፈቱ ማድረግ፣
- ሀብት በማሳወቅና በመመዝገብ በጤና ቢሮ ተቋማት የግልፀኝነትና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን ማድረግ፣
- የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንና መላውን ሰራተኛ የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማስቻል፣

### የህግ አገልግሎት ስራ ክፍል

- የግልፅነትና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍንና የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ተገቢዉን ጥረት ማድረግ እንዲሁም ህግ ተጥሶ ሲገኝ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ መከታተል፣
- ከመ/ቤቱ ሰራተኞችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የሙስና ወንጀሎች ላይ የሚያገኟቸውን መረጃዎችና ጥቆማዎች መሠረት በማድረግ ምርመራ እንዲካሄድ፣ ክስ እንዲመሰረትና ውሣኔ እንዲያገኝ የህግ አግባብ በሚፈቅደው ሁኔታ መከታተልና ምክር መስጠት።
- በአጥፊዎች ላይ ከሚወሰነው ቅጣት ባሻገር በሙስና ወንጀል የተዘረፉ ሀብትና ንብረቶችን በማስመለስ ረገድ የበኩሉን ድርሻ መወጣት፣
- ሠራተኞች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በሚያደርጉት ጥረት ለተለያዩ ጥቃቶች እንዳይጋለጡ ተገቢዉን የህግ ከለላና ጥበቃ የሚያገኙበትን ህጋዊ መሰረት ላይ የማማከር ሥራን ትኩረት ሰጥቶ ማከናወን፣
- ከፀረ-ሙስና ስራ ክፍልም ሆነ ከሌሎች አካላት ያገኘዉን መረጃ ወይም የተቀበለዉን ጥቆማ በሚመለከት ያለበትን ደረጃ በየጊዜው የማሳወቅ ሲጠናቀቅም ለሰራተኛዉና ለፀረ-ሙስና ስራ ክፍል ሪፖርት ማድረግ፣

- ይህ ተግባር በከፍተኛ ጥንቃቄ፣ ጥራትና በላቀ ሥነምግባር መካሄድ ያለበት ስለሆነ ህግን መሰረት ያደረገ እገዛ ያደርጋል፣

- ከዚህ አንፃር ስራ ክፍሉ ራሱን ከሙስናና ብልሹ አሠራር በማንፃትና ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት በመስራት ሚናውን በአግባቡ ይወጣል፣

የዉስጥ ኦዲት ሥራ ክፍል

- ለሥራ ማስፈፀሚያ የሚመደብ በጀት በትክክል ሥራ ላይ እየዋሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ የበኩሉን ሙያዊ ኃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት:—

- ከሙስና እና ብልሹ አሠራር በፀዳ መልኩ በሙያዉ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ይሠራል፣ በሙያዉ መርምሮ ያገኘዉ የኦዲት ግኝት መሰረት መስተከስከል ያለባቸዉ እንዲስተካከሉ፣ ያልተሚሉ ሰነዶች እንዲሟሉ፣ የሚታረሙ ግድፈቶች እንዲታረሙ፣ ለህግ የሚቀርቡ ጉዳዮች ለህግ እንዲቀርቡ ለመደረግ ከበላይ አመራር ጋር ይመካከራል፣

- የኦዲት ግኝት ዉጤቱን ሪፖርት በማድረግ ነቄፌታ ያለባቸዉ፣ ግልፅነት የሚጎድላቸዉ፣ ለይቶ ያሳያል፣ መረጃ ለሚፈልግም በህግ አግባብ (ማዕቀፍ) የመረጃ ነፃነት አዋጅን መሰረት አድርጎ ለተገቢ አካል የመስጠት ኃላፊነት ይወጣል፣

- ብልሹ አሠራሮች እንዲታረሙ፣ መልካም አፈፃፀሞች ደግሞ እንዲበረታቱና በሌሎች ልምድ እንዲወሰድባቸዉ ያደርጋል፣

- የውስጥም ሆነ የዉጭ የኦዲት ግኝት ሲመረመር የጉድለቶቹ ምክንያቶች ይለያል፣ መንስኤያቸዉ፡- የሙስና ፣ የእዉቀት ማነስ፣ የሙያ እና የልምድ ማነስ መንስኤ ያለባቸዉን በመለየት በስልጠና፣ በምክርና በድጋፍ የሚታረሙትን እንደየሁኔታዉ መፍትሔ የሚሆኑ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያማክራል፣

- ስለዚህ የውስጥ ኦዲት ሥራ ክፍል በስነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ሥራ ክፍል የጥምረት ኃይል ውስጥ በመሳተፍ የጋራ ጉዳይ አቋም ይዞ መታገል ይኖርበታል፣

<u>የተቋማዊ ለዉጥ/መልካም አስተዳደር ስራ ክፍል</u>

- አሰራሮች የግልጽነትና የተጠያቂነት መርህን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲተገበር ማድረግ፣
- ለመልካም አስተዳደር ጠንቅ የሚሆኑትን የሙስና እና ብልሹ አሠራርን መታገል፣

- ዜጎች የሚፈልጓቸውን አገልግሎቶች ሳይንገላቱ እንዲያገኙ የሚያስችሉ አሰራሮችን ማመቻቸት፣

- ውስጣዊና ዉጫዊ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ተለይተዉ በአጭር፣ በመካከለኛና በረዥም ጊዜ ቅደም—ተከተል እንዲፈቱ አቅጣጫ በማስቀመጥ በቀጣይነት እና በቅንጅት መስራት፣

- የዜጎች ቻርተር አተገባበር ላይ የሚታዩ ክፍተቶች እንዲቀረፉና እንዲስተካከሉ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

- የተቋሙ የአገልግሎት አሰጣጥ ለተገልጋይ ደንበኞች ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ ደንበኞች የሥራ አስፈፃሚዎችን የሥራ ክፍሎች በቀላሉ የት የት እንደሚያገኙዋቸው አመላካች ጽሑፎች በጊቢው ውስጥና በየወለሉና ክፍሉ ግልጽ አድርጎ የሚያሳይ መረጃ እንዲኖር በቂ ማረፊያ እንዲያገኙ ክትትል ማድረግ፣

- ዜጎች መብታቸው እንዲከበር ፍትሐዊ አገልግሎት እንዲያገኙ፣ የግልጽነትና የተጠያቂነት መርሆዎች እንዲከበሩ በማድረግ፣ ከሁሉም በፊት ደግሞ የተቋማዊ ለዉጥ ሥራ ክፍል ራሱን ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዳ በማድረግ አርአያ ሆኖ የሁሉም የሥራ ክፍሎች አገልጋዮች ሙስና የሚያስከትለውን የመልካም አስተዳደር ችግር ተገንዝበዉ በፅናት በመታገል ሚናቸውን እንዲወጡ የበኩሉን ክትትልና ድጋፍ ያደረጋል፣

- ስራ ክፍሉ ሚናቸውን በአግባቡ ይወጡ ዘንድ ደግሞ ከሌሎች የፀረ-ሙስና ተዋንያን ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት ይኖርባቸዋል። ይህም በንድፈ ሀሳብ እና በተጨባጭ ተግባር ስኬታማ እንዲሆን እና በጤና ቢሮ የሚታዩ መልካም ልምዶች ተቀምረዉ በአርአያነት እንዲታይና ተግባራዊ ዉጤቱ እየጎለበተ ለሌሎች አካላት በሞዴልነት እንዲታይ ማድረግ ይገባል።

**ተጣረነት፡-** የጥምረቱ ተጣረነት ለክቡር ቢሮ ኃላፊ ይሆናል።

**የሥራ ስፋቱ፡-** ጥምረቱ ተገባራዊ የሚደረገበት በጤና ቢሮ ፣ ተጣሪ ተቋማት ላይ ይሆናል እንዲሁም በተዋረድ ባሉ ጤና ተቋማት (ሆስፒታልና ክሊጀ)

**የግኑኙነት አገባብር፡-** የአራቱ (4) ጥምረት ግኑኙነት አገባብ በየሩብ ዓመት መጨረሻ ወር የተሰሩ ሥራዎች ሪፖረት ከቢሮ ኃላፊዎች ጋር ሆኖ በመገምግም ለቀጣይ ጊዜ የተኩረት አቀጣጫ የሚሰቀመጡ ሆኖ 4ቱ አባላት ሳያቋረጡ ሥራችዉ ያከናዉናሉ።

# የድርጊት መርሃ ግብር

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ተግባራት | የሚከናወኑበት ጊዜ | ፈፃሚ | አስፈፃሚ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የጥምረቱን አባላት ማደራጀትና ምስረታ ማካሄድ | 19/12/2017 | የስነ-ምግባር ስራ ክፍል | በቢሮዉ |
| 2 | የመነሻ ዕቅድ ማዘጋጀት | 20-22/12/2017 | የስነ-ምግባር ሥራ ክፍል | በቢሮዉ |
| 3 | የተዘጋጀዉን ዕቅድ በጥምረቱ አባላት ማፀደቅ | 23-25/19/2017 | የጥምረቱ አባላት | በቢሮዉ |
| 4 | ዕቅዱን ለስራ አስፈፃሚዎች መላክ | 26/12/2017 | የስነ-ምግባር ሥራ ክፍል | የስነ-ምግባር ሥራ ክፍል |
| 5 | የውይይት መነሻ ፅሁፍ ለሁሉም ስራ አስፈፃሚዎች እንዲደርስ ማድረግ | 27/12/2017 | የስነ-ምግባር ሥራ ክፍል | የስነ-ምግባር ሥራ ክፍል |
| 6 | በተቀመጠው መርሀ ግብር መሰረት ውይይቱ እየተከናወነ መሆኑን መከታተልና ሪፖርት መቀበል | 28-29/12/2017 | የስነ-ምግባር ሥራ ክፍል | የስነ-ምግባር ሥራ ክፍል |
| 7 | የተጠቃለለ የጥምረት አፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት | 30/12/2017 | የስነ-ምግባር ሥራ ክፍል | የስነ-ምግባር ሥራ ክፍል |
| 8 | በሪፖርቱ ላይ የጥምረቱ አባላት እንዲወያዩበት ማድረግ | 1/13/2017 | የስነ-ምግባር ሥራ ክፍል | በቢሮዉ |

**የሥነ-ምግባር መከታተያ**

ስም------------------

ፊርማ------------------

ቀን------------------

**ኦዲተር ዳ/ዳይሬክተር**

ስም------------------

ፊርማ------------------

ቀን------------------

**ህግ ክፍል**

ስም------------------

ፊርማ------------------

ቀን------------------

**ተቋማዊ ሳዉጥ/መልካም አስ/ር**

ስም------------------

ፊርማ------------------

ቀን------------------

ኡስማን አብዱላሂ ኩምሳ
Usman Abdulahi Kumsa

**ክቡር ቢሮ ኃላፊ**

ስም------------------

ፊርማ------------------

ቀን------------------

ወልተጂ በጋሎ ባንጄሬ
Waltaje Begalo Banjere
የጤና ቢሮ ኃላፊ
Head of Health Bureau